# ሁለተኛ እዚህ እንዳይረግጥ እግርሽ

የብርሃኑ ሎሌ ብርቱካን ሚዴቅሳ
ያንገፈግፈኛል ስምሽን ሳነሳ
ድሮስ ማን መረጠሽ ከብርሃኑ በቀር
በትንሹ አየነው ያንቺ በስልጣን መስከር፡፡

በጣም ያሳዘኑኝ አንቺን ለማዳን
ብዙ ወጣት ልጆች በስምሽ አጣን
ወደ እዚህ ለመምጣት ሩጫ አብዝተሽ
መቼ አስታወስሻቸው ለተሰዉልሽ፡፡

በሊሞ መንሸርሸር መዝናናት ለምደሽ
በዘፈን ጭፈራ ስትናጭ ከርመሽ
በየደረሽበት መዋሸት አብዝተሽ
አገርሽ ስትገቢ ሊፈላ ነው ጉድሽ፡፡

ብርሃኑን ያመመው ቫይረሱ ይዞሽ
አስር ጊዜ ይቅርታ እዚህ ያስጠየቀሽ
መቶ እስረኛ ብቻ ላንቺ ከታየሽ
ቆራጥ ጀግና መሪን ኃይሉን ከከዳሽ
የወያኔን መንገድ ጨርቅ ያድርግልሽ፡፡

እንግዲህ ስራሽን ዓለም ካወቀለሽ
ጋሼ ጋሼ ማለት ለምንም አይጠቅምሽ
ከወያኔ ግቢ ጓዝሽን ጠቅልለሽ፡፡

እምቧይ ኮለል ኮለል የባንዶች ጨዋታ
ተግባርሽ መስክሮ የማታ የማታ
ስራሽ ሁሉ ጥፋት ከሆነ ቱማታ
የጠራሽ ባንዳ ነሽ ሚስጥርሽ ተፈታ፡፡

ልብስ መሽማመቱ በሊሞ ሽርሽር
ጭፈራው ሁካታው ጸጉር ማሰማመር
የተጻፈልሽን ታሪክ መቀባጠር
ይቅርታ መጠየቅ ከነሱው ለማደር
እዚያም እኮ ማድረግ  ትችይ ነበር፡፡

ያንቺ ጠበቃነት የዳኝነትሽ
ለወያኔ እንጂ ለሕዝብ ካልጠቀምሽ
እጅግ ያሰፍራል የባንዳ ስራሽ
ሁለተኛ እዚህ እንዳይረግጥ እግርሽ
ፍርዱን ተቀበይው አገርሽ ገብተሽ፡፡

ገነት በቀለ ኪዳነማርያም
ከቶሮንቶ፤ ካናዳ
ኖቬምበር 17 ቀን 2000 ዓ.ም